# ቀጣፊ በራሱ ላይ ይመሰክራል!

*በላይነህ አባተ* (abatebelai@yahoo.com)

*“Ethiopian “President” ….. arrived here last night. During his visit to the kingdom, he will have the regular medical checkup he is used to have in the kingdom” Saudi press Agency http://www.spa.gov.sa/English/search.php?pg=1&s=Ethiopia&by1=n accessed on 7/23/2010)*

*አዎ የኢትዮጵያ ፕሬዘዳንት ነው ያሉት! (በእነሱ አይፈረድም እኛ ፕሬዘዳንት ብለን ስለምንጠራቸው ነው*።) ቀጥሎም “ የተለመደውን የህክምና ክትትል እንደሚያደርጉ” አስታወቀ። “እኔን! እኔ..ን!” ይሉ ነበር አሉ ቀኛዝማች ሰውነቴ የሚባሉ ቅኔ ዘራፊ መኳንንት እንደዚህ አይነት ጉድ ሲገጥማቸው።*

መቼም በዚች ምድር ላይ ይነስም ይብዛም የማይዋሽ ወይም የማይቀጥፍ ሰው አለ ብዬ አላምንም። እንዲያውም ፕሮፌሰር ሮበርት ፌልድማን የተባሉ ተመራማሪ ከሃያ አምስት አመታት በላይ በውሸት ላይ ባደረጉት ጥናታቸው የማይዋሽ ሰው እንደሌለ አረጋግጠዋል። [1] ነገር ግን የውሸት ወይም የቅጥፈት ደረጃ-ደረጃና መልክ-መልክ አለው። በልብ “ሽፋፋ ወይም አመዳም” ብለው እየተሳደቡ በምላስ “አምሮብሻል (you look pretty)” ብሎ ማንቆላጳስ ቅጥፈት ነው (ነገር ግን ብዙም ጉዳት የሌው ውሸት)። ሆዱን ርሃብ እየሞረሞረው ያለ አበሻ ብላ ሲሉት “ጠግቢያለሁ” ብሎ ሲግደረደር መዋሸቱ ነው። ነገር ግን ከራሱ በስተቀር ሌላውን የማይጎዳ ውሸት። ከሚገድል ሰው ለማምለጥ ወደቀኝ የታጠፈን ሰው “በግራ በኩል ሄደ” ብሎ ሊገድል አባራሪውን ማሳሳት ውሸት ነው( ነገር ግን የሰው ህይወት ለማትረፍ የሚዋሽ ውሸት)። በሌላ በኩል ደግሞ ሰው ለመግደል ወይም ለማሰር ሆን ብሎ ወንጀል መፍጠር(በተውሶ ቋንቋ መፈብረክ) ወይም ደግሞ በሐሰት መመስከር በምድርም በሰማይም ሲያስኮንን የሚኖር፤ እጅግ የሚዘገንን ቅጥፈት ነው። ታዲያ ልብ ብላችሁ ከሆነ ብዙውን ጊዜ ቅጥፈትን የህልውናው ምሰሶ ያደረገ ሰው ቀጣፊነቱን በትክክል የሚያረጋግጠው ሌላ ሳይሆን ራሱ ቀጣፊው ነው።

በአገራችን ሕዝብን መርጦ ባልተፈጠረበት ጎሳ ከፋፍለው በማናከስ ላይ ያሉ ከንቱዎች “ምርጥ የሆነ የትምህርት ሥርዓት ዘርግተናል” እያሉ የሰሚን ጆሮ ሲያቆስሉ ይውላሉ። ወዲያው የተናገሩት በኖ ሳይጠፋ (መሬት ሊነካ እንኳን አይችልም) ከውጭ አገር ትምህርት ቤቶች ዲግሪ አገኘን ብለው እውቀታቸውን ሳይሆን ከድሃ መቀነትና የተቀደደ ኪስ በተገፈፈ ገንዘብ የገዟቸውን “የምስክር ወረቀቶች” ያሳያሉ። ይህም ብቻ አይደለም። እንኳን ልጆቻቸውን ዘመድ አዝማዳቸውንም “ምርጥ ሥርዓተ-ትምህርት” ብለው በግድ በሕዝብ ላይ እንደ ቆሌ በጫኑት ወይም በጎጥ ልጓም በሸበቧቸው ትምህርት ቤቶች ውስጥ እዲያልፉ አይፈልጉም። እንደሚታወቀው እነዚህ የዘር ፍልስፍና በሽታ የህሊናቸውን አስኳል ክፉኛ የመታቸው በየደርጃው ያሉ ባለስልጣናት የድሃ ጉረሮ እየዘጉ የሰበሰቡትን ፓውንድና ዶላር እያፈሰሱ ልጆቻቸውን በአውሮፓ፣ በአሜሪካና በኤሽያ ትምህርት ቤቶች ያስተምራሉ።

በተመሳሳይ መንገድም “ግሩም የሆነ የጤና መርሃ-ግብር ዘርግተናል!” እያሉ በድፍረት ይናገራሉ ። ታዲያ ወዲያው ዘወር ብለው ሲያይዋቸው ደግሞ በዘመናዊ መንገድ አዋቅረናቸዋል ከሚሏቸው የጤና ተቋማት እንኳን ገብተው ለመታከም ባጠገባቸው ለማለፍም እንደሚዘገንናቸው ይገነዘባሉ። ሌላው ቀርቶ “ሕዝብ ተራበ” እያሉ ከበለጸጉት አገሮች እየለመኑ በከረጢጥ የሚቀበሉትን እርጥባን ሳይቀር በቻርተር አውሮፕላን እየከነፉ በበለጸጉት አገሮች ለመታከም ያውሉታል። ለዘመናት በእነደዚህ አይነት ዘረፋ በከንቱ የሚፈሰው ገንዘብ በደንብ ቢፈተሽና ቢሰላ በአገሪቱ ውስጥ በየመንደሩ ጤና ጣቢያ ለመስራት የሚያስችል የንብረት መጠን ይሆናል። ታዲያ እነሱ በጣታቸው ለመንካት እንኳን የሚፈሩትን እርኩስ ውሃ ለምን ሕዝብ እንዲዘፈቅበትና እንዲዋኝበት ያስገድዳሉ? ይህ ራሳቸው የማይጠቀሙበትና የሚጸየፉት የትምህርትና የጤና “መርሀ-ግብር” ጥሩነቱ ለማን ይሆን?

ኮሌራ አውሮጳውያንንና ኤሽያውያንን በሚፈጅበት በቀድሞው ዘመን “የኮሌራ በሽታ በጀርም አይተላለፍም” ብሎ የሚያምንና የሚሰብክ ማቅስ ቮን ፒተንኮፈር የተባለ ጀርመናዊ ሳይንቲስት ነበር። ይህ ተመራማሪ እምነቱን ለማረጋገጥም የኮሌራውን ጀርም በብርጭቆ ሞልቶ ጨለጠው። [2] ይህ ሳይንቲስት ምንም እንኳ ከእውነት የራቅ እምነት ቢኖረውም የሚያምንበትን በሌሎች ላይ በመጫን ብቻ አልተወሰነም። እርሱም ግንባር ቀደም ተዋናይ ሆኖ በስራ ላይ አዋለው። በእውነቱ ከልብ በመነጨው እምነቱ ሊደነቅ ይገባዋል ባይ ነኝ። “ከመስመር ወጣህ ብላችሁ” አትገስጡኝ እንጅ በኦርቶዶክሱም ሆነ በካቶሊክና ፕሮቴስታንቱ ያሉ ካህናትና እንደዚሁም ፓስተር እየተባሉ የሚጠሩ ሰዎች” ሰንበት በመጣ ቁጥር “እየሱስ ለኛ ሲል ተሰዋ፣ ጴጥሮስ ተሰቀለ፣ ሐዋርያው ጳውሎስም ለክርስቶስ ሲል ጭንቅላቱን ተቀላ ወዘተ” እያሉ ቅዱሳን ይዘውት የነበረውን መስቀል ጨብጠው በእምነት ከደቀቀ ልብና መንፈስ ሳይሆን ከከንፈርና ከምላስ በመነጨ ሰበካ ብቻ ከሚወጥሩን በሆድ ብቻ ሳይሆን በእመነትና በህሊና መገዛትን (ለእውነት ሲሉ እንደ ቅዱሳን መሰዋእት መሆኑም ቀርቶ ማለቴ ነው) በአርአያነት ቢያሳዩ አለም የተወጠረችበት የቅጥፈት ገመድ በላላ ነበር።

የአፍሪካ  በተለይም የኢትዮጵያ ገዥዎች ሲያደርጉት የሚታየውማ እንኳን ህሊና ከለበሰ አእምሮ ከደመነፍስም የመነጨ አይመስልም። ሌላው ቀርቶ ራሳቸው አቋቋምን በሚሏቸው የአገልግሎት መስጫ ተቋማትም ቅንጣት እምነት የላቸውም። ከላይ እንደተገለጠው ድንቅ የሆነ የትምህርትና የጤና ሥርዓት ዘርግተናል እያሉ አይናቸው በጨው ታጥበው ይናገራሉ። ዳሩ ግን በዘረጉት ኩድኩድና እጅግ ኋላቀር በሆነው "የትምህርት ሥርዓታቸው" ራሳቸው፣ ልጆቻቸውም ሆነ ዘመዶቻቸው እንዲያልፉ አይፈልጉም። በተመሳሳይ መንገድ በዘመናዊ መልክ ገንብተናቸዋል በሚሏቸው የጤና ተቋማት ውስጥ መታከም አይሹም። ከድሃ ጉረሮ በሞለቀቁት ገንዘብ ክንፍ እያወጡ በረው ሌላ አገር  መታከማቸው የማይነጥፈውን ቅጥፈታቸውን ያሳያል። አንዱን ትቶ ሌላውን ይረግጣል ብላችሁ አትገስጡኝ እንጅ ሰሞኑን ቦሌ መድሐኒአለም ቅጥር ግቢ ውስጥ የተቆለለው ካብም የተካበለትን ፍጡር ቅጥፈት አደባባይ ከማውጣት በስተቀር ከምድርም ሆነ ከሰማይ ቤት ሲኦል የሚያድን አይመስለኝም። እንዲያው ለመሆኑ ለሰው ልጅ ልእልና ሲሉ አንገታቸው ለሰይፍ የሰጡት እንደ ጴጥሮስና ጳውሎስ ያሉ ቅዱሳን ሐዋርያት ናቸው ወይስ ክርስቶስ ራሱ ሕዝብ በቸነፈር እያለቀ "በቁማችን እንድናየው በአልማዝ፣ በወርቅና በነሐስ ያጌጠ ሐውልት በአስራትና በስለት ገንዘብ አሁኑኑ ገንቡልን!" ያሉት? እኔ እስከማውቀው ድረስ እንኳንስ ክርስቶስና ቅዱሳን ሐዋርያት  ይቅርና መነኩሴዋ አያቴ እንኳን ሐውልትም ሆነ መቃብር ቤት እንዳትሰሩልኝ ብላ ነው ያለፈችው። ከዚህ የምንገነዘበው "አገረ-ገዥዎች ወይም የቤተ-ክርስቲያን አስተዳዳሪዎች ነን" የሚሉት ከንቱዎች የሚዋሹት ሕዝብንና እግዚአብሔርን ብቻ ሳይሆን ራሳቸውንም ጭምር መሆኑን ነው። በተጨማሪም ከእንደዚህ አይነቱ ጉድ የምንረዳው በቀጣፊ ላይ ቃል የሚሰጥ እማኝ ፍለጋ መሄድ ጊዜ ማባከን መሆኑን ነው። ቅጥፈትን የህልውናው መሰረት ያደረገ ሰው እንኳን በይወት እያለ ሞቶም እየደጋገመ በራሱ ላይ ሲመሰክር ይኖራልና።  ከዚህ ያድን! አሜን።


*ዋቢ*

*1. Robert Feldman; The Liars in your life First Edition, 2009*

*2. Life History of Max von Pettenkofer፡ http://jn.nutrition.org/cgi/reprint/107/9/1567*

**ስም አውጡልኝ        http://www.quatero.net/pdf/Sim%20awutu.pdf*


*ሐምሌ ሁለት ሺህ ሁለት ዓ.ም.*